


# መልዕክተ-አራዳ

ይድረስ ለአራዳ ልጆች!.............................................................................ተላከ ከዲበኩሉ!

**ውድ የአራዳ ልጆች ሆይ!**

የከበረ የናፍቆት ሠላምታዬ፤ ውቂያኖስ ሠንጥቆ አድማስ ዘልቆ ባላችሁበት ይድረሳችሁ! ሠላም ባይኖራችሁም! ሠላም ለናንተ ትሁን እላለሁ!።ሠላም ለጦቢያ! ሠላም ለአራዳ!። ሠላምን የማይመኝ፤ ለሰላም የማይዘምር ማን አለ?

**አራዶች ሆይ!** ፈረንጅ አምላኩ እንኳ ሳይቀር ድፍን አራዳ ያጨበጨበለት መልዕክታችሁ ደርሶኝ ተመለከትኩት። መልእክታችሁም በፈረንጅ ሃገር ለሚገኘው ወገን ሁሉ ይደርስ ዘንድ የሠደዳችሁት መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ እናም- አደራችሁን ጠብቄ፤ አንዳችም ሳልጨምር አንዳችም ሳላጎድል ለድፍን የፈረንጅ ሃገር ነዋሪ ወገናችሁ አስተላልፈያለሁ፡፡

"ፈርስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም " ይላሉ፡-እኔም እናንተም የምናውቃቸው አቻምየለሽ። እናም መልዕክታችሁ ደርሷል። እስካሁን ግን ያነበብኩት ወይም የሰማሁት ምላሽ የለም።

ምናልባት!...ወገኖቻችሁ እያሰቡበት ይሆናል። ምናልባት!..በመልዕክታችሁ ቅር የተሰኙ በዝተውም ይሆናል፡፡ ምናልባት!.. ማን በአራዳ ልጆች መልዕክት እጁን ያስገባል ብለውም ይሆናል።ምናልባት!.. ምላሽ ለመስጠት ግዜ አጥተውም ይሆናል።ምናልባት!...የፈረንጅ ሃገርን ህይወት ማን ያውቃል? ለማንኛውም ሁሉም የኔ ግምቶች ናቸው። የግሌ ምናልባቶች ...!

በበኩሌ ግን በመልእክታችሁ ተረብሻለሁ፡፤ ስሜቴ ተነክቷል። ቅሬታዎቻችሁ በፈረንጅ ሃገር በምንገኝ ወገኖች ላይ በርክተዋል።በነኚህ ቅሬታዎቻችሁ ላይ የግሌ የሆነ አስተያየት ቢኖረኝም፡ እንዳው በደምሳሳው ግን "**አራዶች እውነት አላቸው!** " ብያለሁ፡፡

ሆኖም ከኔ መልስ የማትጠብቁ በመሆኑ በመልእክቶቻችሁ ይዘት ላይ በፈረንጅ አገር ያሉ ወገኖቻችሁ የሚሉትን ይበሉ እንጂ እኔ የምለው የለኝም፡፡ ዝም! ድርገም፡፡

ከመልእክቶቻችሁ ውስጥ ግን ገለልተኛ የሆነው አንቀጽ እንደ አንኮበር ቅጠል ለብልቦኛል።

*"አቤቱ ጦቢያ ሆይ ! ለክብርሽና ለአንድነትሽ ጃንጥላሽን ያቆሙት ልጆሽ ወዴት አሉ? እስከመቼስ እጆችሽን ወደ እግዚአብሄር ዘርግተሽ ትጸልያለሽ? ያንቺስ ሙሴ ከተራራ የሚወርደው መቼ ይሆን? ኤሎሄ! ኤሎሄ! አባት ሆይ! ጦቢያን ምነው ረሳሃት?"*

**አራዶች ሆይ!፡-** ከዚህ አገላለጻችሁ በበለጠ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን የሚገኙበትን ሥዕል ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ አባባል ሊኖር አይችልም። ሃቅ ነው መሪር ሃቅ።

ያም ሆኖ ግን ለጦቢያ ክብርና አንድነት(ዣንጥላ)ሊያቆሙ የተነሱ ልጆች በየቦታው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየተጣሩ ነው። ቁምነገሩ ያለው የሚቆመው ዣንጥላ የእንቧይ ካብ አልያም ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ እንዳይሆን በአስተማማኝ ሊሾ መገንባቱ ነው፡፡

እርግጥ ነው ከ1983 ዓ/ም ወዲህ "ኢድሃቅ" "ህብረት" "ቅንጅት" ተመስርተው አይተናል።እነኚህ ድርጅቶች በህዝባችን ትግልና አንድነት ላይ ጥለው ያለፉትን ጠዝጣዥ ቁስል ብናስታምም በዛው መጠን ደግሞ ለነገ ጥንካሪያችንና ሕብረታችን ዛሬ ልንማራቸው የሚገቡንን አሉታዊና አዎንታዊ ጎዳናዎች በማያሻማ መልኩ አስቀምጠው አልፈዋል።

ቁምነገሩ እዚህ ላይ ነው። ተምረናል ወይ? ለለውጥ ከመነሳሳታችን፤ ለለውጥ ሌሎችን ከመጥራታችን በፊት ራሳችን ምን ያህል ተለውጠናል? በተለይ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎቻችን!

ከስህተቶቻችን ከተማርን ያምናውና የካቻምናው ህልማችን እንዳያገረሽ አሁን የተጣለው መሰረት ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ግዜ የሚያሳየን ይሆናል።

**አራዶች ሆይ!** አትጠራጠሩ!- ለኢትዮጵያ ዕንባና ፀሎት አምላክ ምላሽ የሚሰጥበት ግዜ ተቃርቧል።አትጠራጠሩ ኢትዮጵያ ሙሴዋ ወይም ሙሴይቷ ከተራራ የሚወርደበት ወይም የምትወርድበት ግዜ ተቃርቧል።

ለማንኛውም ግን በግንቦቱ ትንንቅ ከወገናችሁት ጋር ወግኜ ከጎናችሁ መቆሜን ታውቁልኝ ዘንድ በዚህ አጭር ደብዳቤ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

ለኢትዮጵያ ትንሣዔ በምታደርጉት ትግል "እመ-ብርሃን" ጽናቱንና ብርታቱን ትስጣችሁ። እንደ አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ አምላክ ከናንተ ጋር ይሁን!

ዘወትር ናፋቂያችሁ ዲበኩሉ! ከባህር ማዶ!